ALERT

## ከአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በግል ሕክምና አገልግሎት የአለርት ስኬታማው ጉዞ !

**ዳንኤል ዘነበ**

አለርት በብዙ ኢትዮጵያን ልብና አዕምሮ ውስጥ ዘወትር የሚታወስ፣ በአፍሪካ አህጉርም በጤናው ዘርፍ ስሙ የገነነ የተቋም ስያሜ ነው:: በሀገራችን ቀደም ካሉ ጊዜያት ጀምሮ ከስጋ ደዌ ጋር ለተያያዙ የጤና ችግሮች መፍትሔ ሲሰጥ ኖሯል:: በዚህ ዘርፍ ብቸኛው የህክምና የጥናትና ምርምር ማዕከል ሆኖ ለዘጠና አመታት ዘልቋል:: አለርት ሆስፒታል ከመነሻው ከስጋ ደዌ ጋር የተያያዙ የጤና እክሎችን ለማከም የተቋቋመ ቢሆንም በሒደት ለሁሉም ዓይነት ታማሚዎች አጠቃላይ የህክምና አገልግሎት መስጠት ጀምሯል:: በተጨማሪም በጤናው ዘርፍ የምርምር ስራዎችን ያከናውናል ፣ የስልጠና አገልግሎትም ይሰጣል::

የአለርት ማዕከል በህክምና እና ስልጠና ዘርፎች ከሚሰጠው ውጤታማ አገልግሎት በተጨማሪ በምርምር መስኩም ከኢትዮጵያ አልፎ ለአህጉሪቱ የተረፉ ስራዎችን አከናውኗል:: በምርምር ስራው ስጋደዌ፣ ቲቢና ሌሎችም በሽታዎች መንስኤና መፍትሔ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሳይንሳዊ ፅሑፎችን በየጊዜው እያሳተመ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል:: በማዕከሉ ከተዘጋጁት የምርምር ፅሑፎች መካከል፣ 12 አመታትን ፈጅቶ በሊፕረሲ ሪቪው ጆርናል ላይ የወጣው ፅሑፍን ጨምሮ በየጊዜው የሚወጡ ጥናቶች ይጠቀሳሉ። በአጠቃላይ ተቋሙ ላለፉት ዘጠኝ አስርት አመታት በህክምና፣ በምርምርና በስልጠና አገልግሎት በርካታ የስኬት ምዕራፎችን መሻገር ችሏል::

በእነዚህ አመታትም አለርት የአገልግሎት አድማሱን ለማስፋት፣ የተገልጋዮችን እርካታና ቁጥር ለመጨመር፣ የአገልግሎት ጥራቱን ለማሻሻልና ተቋማዊ ብቃቱን በማሳደግ አሰራሩን ለማዘመን የተለያዩ ጥረቶችን ከማድረግ ቦዝኖ አያውቅም:: ለአብነትም የተገልጋዮችን እርካታና ቁጥር በመጨመር ረገድ የግል ህክምና አገልግሎት መጀመር ተጠቃሽ ነው:: የግል ህክምና አገልግሎቱን ከአስር ዓመት በፊት የጀመረው አለርት በዘርፉ ስኬታማ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

በዛሬው እትማችን በአለርት ሆስፒታል በግል ህክምና አገልግሎት የሥራ እንቅስቃሴን በተመለከተ ለአለርት ኮንፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የህክምና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለዶክተር ፀጋዬ ገብረሀና ያቀረብንላቸውን ጥያቄ የሰጡንን ምላሽ እንደሚከተለው አዘጋጅተነዋል ።

### የአገልግሎቱ ጅማሮ

በመንግሥት ሆስፒታሎች የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀና በሥርዓት የሚመራ እንዲሆን ለማስቻል የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 167/2001 ማጽደቁ ይታወቃል:: የጤና ሚኒስቴር በመንግሥት ሆስፒታሎች የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያው ወጥቶ በ2007 ዓ.ም በበርካታ ተቋማት አገልግሎቱ ሊጀመር ችሏል::

በመንግሥት ሆስፒታሎች የግል ህክምና አገልግሎት ከጠዋቱ 2 ሰአት ከ30 እስከ 11ሰአት ከ30 ካለው የመደበኛው የስራ ሰዓት ውጪ እንዲሁም ቅዳሜ እና እሁድ ይሰጣል። ይህ አገልግሎት ከመደበኛው አገልግሎት ውጪ ያለ "ሁለተኛ አማራጭ" ተደርጎም ይቆጠራል ።

በመንግሥት ሆስፒታሎች አገልግሎቱ መጀመሩ በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይታመናል። በዋነኝነት የባለሙያዎችን የስራ ተነሳሽነት በመጨመርና ባሉበት ሆስፒታል ረጅም ጊዜ ቆይተው እንዲያገለግሉ ከማስቻሉም በላይ ለህብረተሰቡ አማራጭ የህክምና አገልግሎት ይፈጥራል:: በተጨማሪም በግል ህክምና ተቋማት ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የህክምና ዋጋ ለማረጋጋትም የራሱ ሚና ያጫወታል::

የግል ህክምና አገልግሎት መጀመር ሦስት መሰረታዊ ዓላማዎች ይዟል። ይኸውም ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎችን በመንግሥት የጤና ተቋም ውስጥ ለማቆየት፣የታካሚውን ፍላጎት በመጠነኛ ገንዘብ ማሟላት እና የጤና ተቋማቱ የራሳቸውን ገቢ በማስገኘት አገልግሎታቸውን ማዘመን ናቸው።

በዚህ እሳቤ ከአስር አመት በፊት አለርት ሆስፒታልን ጨምሮ ሌሎች በርካታ የመንግሥት ሆስፒታሎች አገልግሎቱን መስጠት እንዲጀምር ተደርጓል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል እና ከአለርት ሆስፒታሎች ውጪ በአብዛኛዎቹ አገልግሎቱ ቆሟል። አለርት ሆስፒታል አገልግሎቱን በማስቀጠልና በማጠናከር በዘርፉ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ችሏል። ተቋሙ በከፍተኛ ሁኔታ የአገልግሎቱን ተደራሽነቱን አሳድጓል ።

### የተመዘገቡ ውጤቶች

አለርት ሆስፒታል የግል ህክምና አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የአይን እና ቆዳ ህክምና በቋሚነት ፤ የፕላስቲክ ሰርጀሪ እና የጥርስ ህክምና በተቆራረጠ መንገድ ሲሰጥ ቆይቷል። ነገር ግን በሂደት አገልግሎቱን ሰፋ ባለ ሁኔታ መስጠት የሚያስችሉ ሥራዎች በመስራት በ2015 ዓ.ም የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ክፍሎችን ወደ 13 ከፍ ማድረግ ተችሏል። በአሁኑ ወቅትም የግል ህክምና ከድንገተኛ ፣ ከማዋለጃ እና ከጽኑ ህክምና ክፍል ውጪ አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል። ይህም በክፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ተችሏል። ሌላው ከአገልግሎት ተደራሽነት አንጻርም የታሰበው ውጤት የመጣ ሲሆን፤ በግል ህክምና አገልግሎት በተመላላሽ ህክምና ብቻ በወር እስከ ሰባት ሺህ ሰው አገልግሎት እያገኙ ይገኛል። በቀዶ ህክምና ደግሞ በወር እስከ 250 ቀዶ ጥገና ህክምናዎች ይደረጋሉ። በሌላ በኩል በመደበኛው ህክምና በወር እስከ አንድ ሺህ ቀዶ ጥገናዎች ይደረጋሉ። በመደበኛው የህክምና አገልግሎት 40 ሺህ አካባቢ የሚሆን ተመላላሽ ታካሚ ይስተናገዳሉ። በሆስፒታሉ በሚሰጠው የመደበኛ አገልግሎት ላይ ስምንት ሺህ ሰው ጨምሯል።

ከባለሙያ አንጻር የመጣው ውጤት ያለ ሲሆን፤ የህክምና ባለሙያ ካለው የኑሮ ሁኔታ ከሚገኘው ገቢ ማነስ ጋር ተያይዞ የተሻለ ክፍያ ወደሚያገኙባቸው የግል ተቋማት ይፈልሳሉ። ይህም ከፍተኛ የሆነ የባለሙያ ፍልሰት እንዲፈጠር አድርጓል። ቢያንስ ተመጣጣኝ የሆነ ገቢ እያገኘ ባለበት ተቋም ስፔሻሊስት ሀኪም ሌሎች ባለሙያዎችም እንዲቆዩ እና እንዲያገለግሉ ማድረግ ተችሏል። ስለዚህ በሆስፒታሉ የአገልግሎቱ መሰጠት የባለሙያዎችን የስራ ተነሳሽነት በመጨመርና ባሉበት ሆስፒታል ረጅም ጊዜ ቆይተው እንዲያገለግሉ ከማስቻሉም በላይ ለህብረተሰቡ አማራጭ የህክምና አገልግሎት ሆኗል። በተጨማሪ በግል ህክምና ተቋማት ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የህክምና ዋጋ ለማረጋጋትም የራሱን ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

### የአለርት ስኬት ምንጭ

አለርት ሆስፒታል ለዚህ ውጤት እንደምክንያት የሚያስቀምጠው አገልግሎቱ የራሱ አደረጃጀት ያለው እና አስተዳደራዊ ስራውም ከመደበኛው ጋር የተለየ እንዲሆን በመደረጉ ነው። ከሆስፒታሉ የተለያዩ ክፍሎች የተውጣጡ ባለሙያዎች ያካተተ የግል ህክምና አገልግሎት ኮሚቴ እንዲቋቋም ተደርጓል። የግል ህክምና ኮሚቴው በየእለቱ በመገናኘት በመደበኛ እና በግል ህክምና የሚሰጠውን አገልግሎት ኦዲት ያደርጋል። የአገልግሎት አሰጣጡን ይቆጣጠራል ይገመግማል። በዚህ አንድ ታካሚ ከመደበኛ ህክምና ወደ ግል ህክምና አገልግሎት ሲገባ ተገፍቶ እንዳልሆነ ፤ አገልግሎት አጥቶ እንዳልሆነ የአገልግሎት ጥራቱ የተለየ በመሆኑ እንዳልሆነ እንዲረጋገጥ ይደረጋል። ታካሚው



ዶክተር ፀጋዬ ገብረሀና

ከመደበኛ የህክምና አገልግሎት ወደ ግል ህክምና ሲመጣ የሚፈርመው የስምምነት ሰነድ አለ። ሰነዱ አምኖበት ምንም ጫና ሳያድርበት መደበኛው ላይ መጉላላት እንደማይኖርበት በቂ አገልግሎት ማግኘት እንደሚችል አውቆ ወይም ደግሞ ካለው ጊዜ አንጻር በግል ህክምና ብገለገል ይሻለኛል ብሎ መርጦ ብቻ እንደሆነ የሚታይበት ነው ።

ሌላው ከግል ህክምና አገልግሎት ጋር ተያይዞ የወጡ ደንቦች (ማለትም በመደበኛ የማይሰጥ አገልግሎት በግል ህክምና አገልግሎት መስጠት አይቻልም ፣ ሁለተኛው የትኛውም አይነት አገልግሎት በመደበኛም ሆነ በግል ሲሰጥ ተመሳሳይ መሆን አለበት የሚል ነው:: ኮሚቴው የእነዚህ ደንቦችን ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል። በዚህ መንገድ አለርት ኮንፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጠንካራ ስራ ሰርቷል። ይህ በመሆኑም ሆስፒታሉ አገልግሎቱን በማስቀጠልና በማጠናከር በዘርፉ ተጨባጭ ውጤት አምጥቷል።

### እንደ መውጫ

በአጠቃላይ በመንግሥት ሆስፒታሎች የሚሰጠው የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ይህ ውስንነት የተለያዩ መንስኤዎችን መጥቀስ ይቻላል:: በተለይ አገልግሎቱ የራሱ አደረጃጀት የሌለው መሆኑና አስተዳደራዊ ስራውም ከቀኑ ጋር የተለየ አለመሆን ጎልቶ ሊጠቀስ የሚችል ነው::

ይህን ውስንነት ለማስተካከልም ተቋማትም ሆነ መንግሥት ኃላፊነት አለባቸው:: ተቋማቱ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት መስጠት ለአብነትም የግል ህክምና አገልግሎት የራሱ ኮሚቴ እንዲኖረው ማድረግና በዚህ አግባብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

በመንግሥት በጥቂት የመንግሥት ሆስፒታሎች ከመደበኛ ሰዓት ውጪ የሚሰጠውን የግል ህክምና ለማሻሻልና አገልግሎቱን በሁሉም የጤና ተቋማት በስፋት እንዲጀመር መደገፍ ይኖርበታል። በአገልግሎቱ ላይ ከተጠቃሚው፣ከተቋሙና ከባለሙያዎች የሚነሱ ቅሬታዎችን በመፈተሽ ማሻሻያዎች ማድረግ የሚያስችል ስራ ሊሰራም ይገባል።